# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)

## Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

**የካቲት 2 ቀን 2004 ዓ. ም**

## ኢህአፓ አሁንም ከኢትዮጵያ ሙስሊም ወገኖቻችን ጎን መቆሙን ያረጋግጥል።

የወያኔ ቡድን ሥልጣኑን ከጨበጠበት ጊዜ ጀምሮ ተደላድሎ ለመቀጠል እንዲያስችለው በተለያዩ የሃይማኖት ተቋማት ላይ መዝመቱ ይታወቃል። ባጠቃላይ የሃይማኖት ተከታዮችን መብት እየረገጠ፤ የሃይማኖት አባቶችን በተለያዩ ተጽእኖዎች የሱ ታማኝና ተከታይ እንዲሆኑ ለማድረግ፤ የሃይማኖት ተቋማቱን ደግሞ ለፓለቲካ መጠቀሚያነት ለመገልገል ሲጥር መቆየቱ በገሃድ የሚታይ ነው። በቅርቡ በብዙሃኑ የኢትዮጵያ ሙስሉሞች ላይ ባደረገው የመብት መጣስ ከፍተኛ ተቃውሞ ያጋጠመው ሲሆን ይህንን ተቃውሞ ለመግታት አሁንም ከፍተኛ የመከፋፈል ተንኮል እያካሄደ ይገኛል።

ገና ሥልጣን ሲይዝ በብሔር መብት ስም የጀመረው የከፋፋይነት መርዝ እየረከሰበት፤ ተቀባይነት እያጣ ሲመጣ አሁን ደግሞ በሃይማኖት ተቋማት ውስጥ ጣልቃ በመግባት የክፍፍል ስልቱን በአዲስ መልክ ቢቀጥልበትም፤ ይህንን በብርቱ የሚቃወሙ የአወሊያና የሌሎችም ትምህርት ቤቶች እስላም ተማሪዎችና ወጣቶች መብታቸውን ለማስከበር እንዳለፈው ትውልድ ሁሉ ከፍተኛ ተቃውሞ ሲያደርጉ ቆይተዋል። የተማሪዎችንና ባጠቃላይም የሙስሊሙ ወገናችንን ጥያቄዎች በአግባቡ በመመለስ ፋንታ የወያኔ ቡድን የአፈና ተግባሩን አጠናክሮ እየገፋበት ነው። መምህራኖቻቸው ያላግባብ ከሥራቸው ተባራዋል፤ አንዳንድ የእስልምና ሙሁራንም በተለያዩ ቦታዎች ታስረዋል። ይህንን አስከፊና መብት ረጋጭ የወያኔን እርምጃ ዝም ብለው መመልከት ያልቻሉት የአወሊያና እንዲሁም የሌሎች ትምህርት ቤቶች እስላም ተማሪዎች የተቃውሞ እንቅስቃሴ በተጠናከረ መልክ በመካሄድ ላይ ይገኛል።

ኢህአፓ እስከዛሬ ድረስ መብቱ ተገፎ ከቆየውና አሁንም ለመብቱ እየታገለ ካለው ከሙስሊም ኢትዮጵያዊ ወገናችን ጎን አብረን እንደምንሰልፍ በዚህ አጋጣሚ ልናረጋግጥ እንወዳለን።

የኢትዮጵያ ሙስሊም ወገኖቻችን መብት በማያሻማ መንገድ ሊከበር የሚችለው የሁሉም ኢትዮጵያውያንን መብት የሚያስከብር ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በሕዝቡ የሥልጣን ምንጭነት ሲመሠረት ስለሆነ፤ ይህንን ሥርዓት ለመመሥረት ለሚደረገው እልህ አስጨራሽ ትግል በተጨባጭ ትብብር ትግሉን ማጠናከር ከመቼውም ጊዜ በላይ አሁን ነው እያልን የትግልና የትብብር ጥሪያችንን እናቀርባለን።

መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በነፃ ድርጅቱ ዙሪያ በመሰልፍና የጋራ ትግሉን በማጠናከር የመብቱ ባልቤት እንደሚሆን አንጠራጠርም!

እናቸንፋለን!


**EPRP**
P.O.Box 73337
Washington D.C. 20056
U.S.A
Tel. : (202) 291-4217
Fax : (202) 291-7645

**EPRP**
BP 22
Bois Colombes 92270
France

**E-mail** ESPIC@aol.com **Website:** http://www.EPRP.com